## ያግኙን

ስልክ፡- 011 515 08 82
ፋክስ፡- 011 552 64 11
ፖ.ሳ.ቁ፡- 717
ዌብ ሳይት፡- WWW.nala.gov.et
ፌስቡክ፡- Ethiopian National Archives and Library Agency-ወመዘክር
የኦንላይን ድህረ ገጽ፡- WWW.wemezeker.nala.gov.et
ቴሌግራም፡- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት አገልግሎት
ዩ ቲዩብ፡- ወመዘክር National Archive and Library of Ethiopia
የጥሪ ማዕከል፡- 888


ከ1936 ዓ.ም ጀምሮ

# ስለ ህትመተ ኢትዮጵያ የስራ ክፍል እናስተዋውቆት!

ከአንድ ሀገር ማህበራዊ፣ ታሪካዊ፣ ባህላዊ፣ ፓለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ክንውኖች ጋር በተያያዘ የሚታተሙ ማናቸውም ህትመቶች ተሰባስበው፣ ተደራጅተውና ተጠብቀው ለትውልድ እንዲተላለፉ እና በጥንቃቄ (Closed Accessed) አገልግሎት ላይ መዋል እንዲችሉ ከህግ የመነጨ ሥልጣን ያለው አካል ይህን ተልዕኮ እንዲወጣ ይቋቋማል፡፡ እስከ 20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ድረስ የተለያዩ ሀገራት ብሔራዊ ቤተመጻሕፍት ትኩረት የህትመት ውጤቶችን የማሰባሰብና በህግ ክምችት ክፍላቸው ጠብቀው ለትውልድ ማስተላለፍ ላይ የነበረ ሲሆን አሁን ባለንበት 21ኛው ክፍለ ዘመን የበርካታ ሀገራት ብሔራዊ ቤተመጻሕፍት አዋጆቻቸውን በማሻሻል ዲጂታል ህትመቶችንና ሰነዶችን አሰባስቦ ለትውልድ ማስተላፍም ሌላው የትኩረት መስክ እንዲሆን አድርገዋል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት አገልግሎት የተለያዩ ዘርፎች የንባብ አገልግሎት፣ የጥናትና ምርምር አገልግሎት፣ የሪከርድ ሥራ አመራር፣የመዛግብት ሙያዎች ስልጠናና የማማከር አገልግሎት፣የሪፈረንስ አገልግሎት ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች በጣም ጥቂቶቹ ሲሆኑ በህዝብ ቤተመጻሕፍት አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ስር የሚገኘው የህትመተ ኢትዮጵያ (Legal Deposit) የስራ ክፍል ልዩ ልዩ የህትመት ክምችት የያዘ ነው፡፡

በበርካታ የዓለማችን ሀገራት ይህ ዓይነቱ ተልዕኮ ለብሔራዊ ቤተመጻሕፍት ይሰጣል፡፡ በእኛም ሀገር የህትመተ ኢትዮጵያ /Legal Deposit/ ተቋማችን በአዋጅ 179/91 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የሚሰባሰቡ ህትመቶችን አደራጅቶ ለቀጣይ ትውልድ ለማስተላለፍና አገልግሎት ላይ ለማዋል የተቋቋመ ክፍል ነው፡፡ አሁን በሥራ ላይ የሚገኘው የተቋማችን አዋጅ ህትመቶችን በተቋማችን ስለማኖር በሚከተለው መልኩ በግልጽ ይደነግጋል፡፡

አንቀጽ 19፡- ህትመቶችን የማኖር ግዴታ

1. ማንኛውም አታሚ ወይም አሳታሚ ያተመውን ወይም ያሳተመውን ማንኛውም አይነት ህትመት ቅጂ በድርጅቱ የማኖር ግዴታ አለበት።
2. ውጪ ሀገር ተዘጋጅተው ኢትዮጵያ ውስጥ የተባዙ ሥራዎች አዘጋጅ ወይም አከፋፋይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገውን የማክበር ግዴታ አለበት።
3. ማንኛውም አሳታሚ ወይም ደራሲ በሙሉም ሆነ በከፊል ኢትዮጵያ ውስጥ ተዘጋጅተው ውጪ ሀገር የታተሙ ህትመቶችን 3 ቅጂ የማኖር ግዴታ አለበት።

አንቀጽ 20፡- ህትመቶችን የማኖሪያ ጊዜና ሁኔታ

ህትመቶችን የማኖር ግዴታ የተጣለበት ማንኛውም አታሚ፣ አሳታሚ፣ ደራሲ፣ አባዢ ወይም አከፋፋይ ህትመቶችን ህትመቱ ከተጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ በአደራ ፖስታ ወይም በልዩ መልዕክተኛ ለድርጅቱ ቤተ መጻሕፍት ማስረከብ አለበት።

የህትመተ ኢትዮጵያ የስራ ክፍል እድሜ ጠገብ መጻሕፍት፣ጋዜጣ፣መጽሔት፣ፖስተር፣ፍላየር እና የተለያዩ የጽሑፍ ስራዎችን ጠብቆ ለማቆየትም ሆነ ለአገልግሎት በሚመች መልኩ አዘጋጅቶ አንባቢያንን የሚያስተናግድ ክፍል ነው። በህትመተ ኢትዮጵያ ያሉ የጽሑፍ መረጃዎችን ተማሪዎች፣ ጥናት አጥኚዎች፣ ተመራማሪዎች፣ የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ባለሙያዎች፣ ደራሲያንና ሌሎችም የአገልግሎቱ የዘወትር ተጠቃሚዎች ናቸው። በዚህ ክፍል ለተለያዩ ሀገራዊ፣ ማህበራዊ፣ የትምህርታዊ መስክና ታሪካዊ ጥናቶች መነሻም ሆነ ግብአት የሚሆኑ ከግማሽ ክፍለ ዘመን በላይ የቆዩ የጽሑፍ ሀብቶች ይገኛሉ። ደራሲያን መጽሐፋቸውን በድጋሚ ለማሳተም ፈልገው በገበያም ላይ ሆነ በእጃቸው የመጽሐፉን ኮፒ በሚያጡበት ጊዜ ሁሉ በዚህ ክፍል ውስጥ ተጠብቆ የሚያገኙበት አጋጣሚ ሰፊ እንደሆነ የክፍሉ ባለሙያዎች ይናገራሉ።

በህትመተ ኢትዮጵያ አንድ ሁለት ብለን ዘርዝረን የማንጨርሳቸው የተለያዩ የህትመት ውጤቶች ሲኖሩ በ1948 ዓ.ም ከግዕዝ ወደ አማርኛ ከተተረጎመው "ኢትዮጵያዊያን ፈሎሶፈዎች ሐተታ ዘ ዘርአያዕቆብ" ጨምሮ ከ1930ዎቹ ጀምሮ የታተሙ የታሪክ፣ የሀይማኖት፣ የግብረገብ፣ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ህይወት፣ ፖለቲካዊ፣ቤተሰብ፣ስነ ልቦና፣ ልብወለድ፣ ግጥሞችና ሌሎችም ዘውጎች በስብስቡ ውስጥ ሲገኙ ፣የ1930ዎቹ አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ የ1930ዎቹ ሰንደቃላማችን ጋዜጣ፣ በንጉሱ ዘመነ መንግስት በግዕዝ ፊደላት በኦሮምኛ ቋንቋ ይታተም የነበረው በሬሳ ጋዜጣ፣ የ1930ዎቹ የኤርትራ ድምፅ ጋዜጣ፣ የ1940ዎቹ የኢትዮጵያ ድምፅ ጋዜጣ፣ የ1940ዎቹ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣የ1940ዎቹ The Ethiopia Herald ጋዜጣ እና ሌሎችም እስከ አሁን የታተሙና እየታተሙ ያሉ ጋዜጦች ፤የ1930ዎቹ ብርሃንና ሰላም መጽሔት፣የ1940ዎቹ መነን መጽሔት፣የ1950ዎቹ Ethiopian Magazine (Asmera) መጽሔት፣የ1960ዎቹ Ethiopian Mirror መጽሔት፣ የ1960ዎቹ Addis Reporter

መጽሔት፣የ1960ዎቹ ጎህ መጽሔት፣ የ1960ዎቹ የስልጣኔ በር መጽሔት፣የ1960ዎቹ የሶቭየት ኑሮ መጽሔት፣የ1970ዎቹ ማርክሳዊ ርዕዮት መጽሔት፣ የ1970ዎቹ የካቲት መጽሔት እና ሌሎችም እስከ አሁን የታተሙና እየታተሙ ያሉ ሀይማኖታዊ፣ የግልና የመንግስት ተቋማት መጽሔቶች፣የ1923 ዓ.ም የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ህገ-መንግስት ዕትም፣ በድጋሚ በንጉሱ በ1948 ዓ.ም የተሻሻለው የኢትዮጵያ ህገ-መንግስት፣ የደርግ ዘመነ መንግስት የኢትዮጵያ ህገ-መንግስት እንዲሁም የኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ-መንግስት እና በተለያየ ቋንቋ የተዘጋጀ የክልሎች ህገ-መንግስት እጅግ በጣም በጥቂቱ የተገለጹ የክፍሉ የመረጃ ሀብቶች ናቸው፡፡

የህትመተ ኢትዮጵያ የስራ ክፍልን አገልግሎት ለማግኘት ማንነትን የሚገልጽ የታደሰ መታወቂያ ብቻ ይዞ መቅረብን ይጠይቃል፡፡ እሁድና በህዝባዊ በአላት ቀን አገልግሎት አይሰጥም፡፡

| **የህትመተ ኢትዮጵያ የስራ ክፍል የስራ ሰዓት፤** | |
|---|---|
| ዘወትር ከሰኞ-አርብ ከጠዋቱ 2፤30- ምሽት 1፤30 ምሳ ሰዓትን ጨምሮ | ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 2፤30- ምሽት 12፤00 ምሳ ሰዓትን ጨምሮ |